የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሠላሳ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፹፭
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No.85
Addis Ababa 28th Jun, 2024

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፸፭/፪ሺ፲፮
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

ገፅ…………………………………………… ፫ሺ፯፻፳፯

CONTENT

Regulation no. 175/2024
Regulation issued to re-establish Addis Ababa City Government Kenema Pharmacies Enterprise

Page…………………………………….….3727

## ደንብ ቁጥር ፻፸፭/፪ሺ፲፮
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት የሰው መድሃኒትና የህክምና መሣሪያ አቅራቦት የጥራት ደረጃቸው የተጠበቀ እና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ ለሰው አገልግሎት የሚውሉ መድሃኒት እና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን ለተገልጋዮች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያቀርብ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ይህም ለህዝቡ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ እና ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን ከወጣው ደንብ ቁጥር ፻፭፱/፪ሺ፲፮ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Regulation no. 175/2024
## Regulation issued to re-establish Addis Ababa City Government Kenema Pharmacies Enterprise

**WHEREAS,** it has become necessary to Addis Ababa City Administration, Kenema Pharmacies eneterprise, in order to supply human medicines and medical equipment, whose quality level is protected and their efficacy is proven, to provide human medicine and medical equipment to users at reasonable prices;

**WHEREAS**, it has become necessary to harmonize it with Regulation No. 159/2016 issued by the Addis Ababa city administration and to determine the conditions under which public eneterprise are managed ; This is due to the significant contribution it makes to the improvement of health service delivery to the people.

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሠን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፮ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና አንቀጽ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅትን እንደገና ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፻፸፭/፪ሺ፲፮ ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. “ደንብ” ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ ነው፤

፪. “ቦርድ” ማለት በደንቡ መሠረት የሚቋቋም የድርጅቱ አንድ የሥልጣን አካል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለድርጅቱ መቋቋምና ዓላማ

**፫. መቋቋም**

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት (ከዚህ በኋላ “ድርጅት” እየተባለ የሚጠራ) የልማት ድርጅት ሆኖ እንደገና በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፤

፪. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለሥልጣን ይሆናል፤

፫ ድርጅቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር ፻፶፱/፪ሺ፲፮ መሠረት ይተዳደራል፡፡

**NOW, THEREFORE**, in accordance with sub Article (2) of Article 68 and sub Article (1) of Article 93 the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 84/2023, the Cabinet of Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This regulation may be cited as “Regulation issued to Re- Establish Addis Ababa City Government Kenema Pharmacies eneterprise Regulation No. 175/2024’’.

**2. Definition**

In this regulation, unless the context otherwise requires:

1. "**Regulation**" shall mean the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024;
2. "**Board**" shall mean a body of authority of the organization established in accordance with the Regulation;

## PART TWO
## THE ESTABLISHMENT AND OBJECTIVE OF THE ENTERPRISE

**3. Establishment**

1. Addis Ababa City Government Kenema Pharmacies eneterprise (hereafter referred to as "Enterprise") has been re-established as a Public Enterprise by this regulation;
2. The Enterprise's Accountability will be to the Administration Authority of Government Public Enterprises of the Addis Ababa City Administration;
3. The Enterprise is administered in accordance with the Regulation issued to Determine, Redefine and Lead the Conditions of Public Enterprise of Addis Ababa City Administration Regulation No. 159/2024.

፬. **ዓላማዎች**

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. ለማንኛውም የመድሃኒት ማዘዣ ይዞ ለሚመጣ ሰው ለጤንነት አስፈላጊ የሆኑ ጥራታቸው፣ ፈዋሽነታቸውና ደህንነታቸው የተረጋገጡ፣ ነፍስ አድንና መሰረታዊ የሆኑ የሰው መድሃኒቶችን፣ የህክምና መገልገያዎችን በዓይነት፣ በመጠንና በተመጣጣኝ ዋጋ ተከታታይነት ባለው መንገድ ማቅረብ፣

፪. የመድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎችን ዋጋ እንዳይንር የገበያ ማረጋጋት መፍጠር፣

፫. በመድሃኒቶችንና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች አስመጪነት ንግድ ስራ ላይ መሰማራት፣

፬. መድሃኒቶችንና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችን ከአስመጪ ድርጅቶችና አምራቾች በመረከብ የጅምላና የችርቻሮ ሥራዎችን መስራት፣

፭. በህብረተሰቡ ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለሚያደርሱ ስር ሰደድ ሕመሞች እና በአጣዳፊ ወረርሽኝ የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመፈወስ የሚያስችሉ መሠረታዊ መድሃኒቶችን ለህብረተሰቡ ማቅረብ፣

፮. በቦርዱ በሚወሰነው መሠረት ከመድሃኒትና ከህክምና መገልገያዎች የሚያገኘውን የተጣራ ትርፍ የጤና አገልግሎት ጥራት ለማሻሻል ማዋል፣

፯. ተጨማሪ የከነማ መድሃኒት ፋርማሲዎችንና መድሃኒት መደብሮችን መክፈት፡፡

፭. **ድርጅቱ እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት የሕዝብ አገልግሎት ግዴታ**

፩. የመድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ግብይት የገበያ ማረጋጋት ሥራ መስራት፣

፪. በከተማው ላይ የሚፈጠሩ ድንገተኛ አደጋዎች ላይ አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፣

፫. በከተማው ላይ የተለያዩ በጎ አድራጎት ተግባራት ላይ መሳተፍ፡፡

**4. Objective**

The Enterprise shall have the following Objectives:-

1. Provide to any individual with a medical prescription can obtain essential medicines and safety medical supplies in the required quantity, consistently and kind, at a reasonable price;
2. Create Market stabilization by controlling price inflation of essential medicine and medical supply;
3. Engage in the business of importing medicines and medical equipment;
4. obtain medicines and medical equipment from importing companies and manufacturers and doing wholesale and retail operations;
5. Provide the public essential medicine caple of preventing and healing chronic and epidemic diseases, which affect the society's health at large;
6. Utilize net profits from pharmaceuticals and medical supplies to enhance the quality of health services as determined by the board's decision.
7. Open up additional kenma pharmacies and pharmaceutical stations.

**5. Public Service Obligation that the Organization is Expected to Provide**

1. stabilize the market to Marketing of drugs and medical supplies;
2. Provide essential support in case of emergencies that affect the city;
3. Engage in various charity activities in the city.

**፮. <u>ካፒታል</u>**

ለድርጅቱ ጠቅላላ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፫፻፴፭ ሚሊዮን ፪፻፳፪ ሺህ ፰፻፴፭ (ሦስት መቶ ሰላሳ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሳ አምስት ብር) ከዚህ ውስጥ ብር ፪፻፶፱ ሚሊዮን ፰፻፵፪ ሺህ ፭፻፪ (ሁለት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሁለት ብር) በዓይነት እና ብር ፸፭ ሚሊዮን ፫፻፹ ሺህ ፫፻፴፫ (ሰባ አምስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰማንያ ሺህ ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር ) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

**፯. <u>ኃላፊነት</u>**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**፰ <u>ዋና መስሪያ ቤቱ</u>**

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በከተማው ውስጥ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፱. <u>ተቆጣጣሪ ባለስልጣን</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

**፲. <u>የድርጅቱ አደረጃጀት</u>**

የድርጅቱ

፩. የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪. አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች፤

፫. ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

**፲፩. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፲፪. <u>የተሻረ ደንብ</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት አደረጃጀትና አሰራርን ለመደንገግ የወጣው ደንብ ቁጥር 31/2002 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**6. <u>Capital</u>**

the authorized capital for the Enterprise is Birr 335,222,835.00 (Three hundred thirty-five million two hundred twenty two thousand eighty hundred thirty five Birr), of which Birr 259,842,502.00 (two hundred fifty nine million eight hundred fourty two thousand five hundred two Birr) has been paid in kind and 75,380,333.00 (Seventy five million three hundred eighty thousand three hundred thirty three Birr) in cash.

**7. .<u>Liability</u>**

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

**8. <u>Head Office</u>**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere in other parts of the city as may be necessary.

**9. <u>Supervisory Authority</u>**

Addis Ababa City Administration Public Enterprise Administration Authority shall be the Enterprise's Supervisory Authority.

**10. <u>Organizational Structure</u>**

The enterprise shall have:

1. Management Board of the Enterprise;
2. A Chief Executive Officer and Deputy Chief Executive Officers as necessary and;
3. The necessary staff.

**11. <u>Duration of the Organization</u>**

The Enterprise is established for an indefinite period duration.

**12. <u>Repealed Law</u>**

Addis Ababa city kenema pharmacy enterprise regulation number 31/2010 are repealed by this Regulation.

፲፫. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

13. **Effective Date**

This regulation shall enter into force as of this 28 day of June, 2024.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of June 2024.**

**ADANECH ABEBE DESA**

**MAYOR OF ADDIS ABABA**